አላሁመ አዑዙ ቢሪዷከ ሚን ሰኸጢክ፣ ወቢሙዓፋቲከ ሚን ዑቁበቲክ፣ ወአዑዙ ቢከ ሚንክ፣ ላኡሕሲ ሠናአን ዐለይክ አንተ ከማ አሥነይተ ዐላ ነፍሲክ"» ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ከቁጣህ በውዴታህ፣ ከቅጣትህ በይቅር ባይነትህ እጠበቃለሁ፤ ከአንተ በአንተ እጠበቃለሁ፤ አንተ እራስህን ያወደስከውን ያህል ላወድስህ አልችልም።" ማለት ነው።

ከእናታችን ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) -አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና- እንደተላለፈው እንዲህ ብላለች፦ «በአንድ ምሽት የአላህን መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከፍራሼ ላይ አጣኋቸው። በዳሰሳ ስፈልጋቸውም
እጄ መስገጃቸው ላይ የተተከለችው የእግራቸው ውስጥ ላይ አረፈች። እርሳቸውም እንዲህ እያሉ ነበር " አላሁመ አዑዙ ቢሪዷከ ሚን
ሰኸጢክ፣ ወቢሙዓፋቲከ ሚን ዑቁበቲክ፣ ወአዑዙ ቢከ ሚንክ፣ ላኡሕሲ ሠናአን ዐለይክ አንተ ከማ አሥነይተ ዐላ ነፍሲክ"» ትርጉሙም
"አላህ ሆይ! ከቁጣህ በውዴታህ፣ ከቅጣትህ በይቅር ባይነትህ እጠበቃለሁ፤ ከአንተ በአንተ እጠበቃለሁ፤ አንተ እራስህን ያወደስከውን ያህል ላወድስህ አልችልም።" ማለት ነው። [ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) -አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና- እንዲህ አለች "ከነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ጎን ተኝቼ ነበር። ሌሊት ላይ አጣኋቸሁ። ቤት ውስጥ ይሰግዱበት የነበረውን ስፍራ በእጄ ዳሰስኩ። በዛን ጊዜም ሱጁድ ላይ ተደፍተው እግራቸውን ተተክለው አገኘሁ። እርሳቸውም እንዲህ እያሉ ነበር: (በውዴታህ) በኔ ላይም ይሁን በኡመቴ ላይ ከምትቆጣው (ቁጣህ) (እጠበቃለሁ) እቃረባለሁ። (ከቅጣትህ) ይቅር ባይነትህ ብዙ ነውና (በይቅር ባይነትህ) (እጠበቃለሁ)። (በአንተ ከአንተ እጠበቃለሁ።) ውብ በሆኑት ባህሪያትህ የልቅና መገለጫ ከሆኑት ባህሪያትህ እጠበቃለሁ። ከአንተ በቀር ከአንተ ለሚመጣው ቅጣት የሚጠብቅ የለምና። ወደ አላህ በመጠጋት ካልሆነ በቀርም ከአላህ መዳኛም መጠጊያም የለም። (በአንተ ላይ አወድሼ አልዘልቅም።) ፀጋህንና በጎ ውለታህን ቆጥሬ መዝለቅ ስለማልችል አንተ የሚገባህንም ውዳሴ በቁጥርም በገደብም ማወደሱን ብጥር እንኳ አልችልም። ለራስህ የሚገባውን በቂ ውዳሴ በራስህ ላይ ያወደስከው አንተ ብቻ ነህና (አንተ ነፍስህን ባወደስክበት ልክ ማወደስ አልችልም።) አንተን የማወደስ ሐቁን በአግባቡ መወጣት የሚችልስ ሌላ አካል ማን አለና?!

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/3566